የ ድ ሬ ዳ ዋ  አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T  G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

4ኛዓመት ቁጥር 19
ድሬዳዋ ጥቅምት30 ቀን
2004 ዓ.ም.

በድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

4th Year No.19
DIRE DAWA 10th october 2011


ማቋቋሚያ አዋጅ

## አዋጅ ቁጥር 19/2004

### የድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ፣ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና ዓላማ በሀገሪቱ ብቁ ተነሳሽነትና የፈጠራ ችሎታው የዳበረ በክህሎት የተካነ የሰው ኃይል በማፍራት ችግር ፈቺ የሆኑ ምርጥ ቴክኖሎጂዎችን የማቀብና የማከማቸት እንዲሁም የመጠቀም አቅምን በመፍጠር በሀገሪቱና በአስተዳደራችን ድህነትን በማስወገድ ለኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ በመሆኑ፣

ይህም ሊሆን የሚችለው በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም ደረጃ ክህሎታቸውን ለማዳበር ለሚፈልጉ ዜጎች ሁሉ በማመቻቸት በመሆኑ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በባህሪው የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሰፊ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ እና ይህንኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በብቃት የሚመራ መንግስታዊ አካል በአስተዳደሩ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

## PROCLAMATION NO 19/2011
### PROCLAMATION TO ESTABLISH TECHNICAL AND VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING AGENCY OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION.

**WHEREAS,** The basic aim of the technical and Vocational Education Training is to produce capable, motivated, innovated and well equipped skilled man power that can enable to maintain and accumulate problem solving best technologies and by creating the capacity to utilize it, shall contribute to the economic development by allievating poverty in the country as well as in the administration,

**WHEREAS**, this can be realized by facilitating high quality of technical and vocational education at all level for those citizens who need to enhance their skills based on need at all economic sectors

**WHEREAS,** the technical and vocational education and tranining by its nature require vast participation

of governmental and non governmental organizations and it is found necessary to esatblish a government body in the administration that directs this technical and vocational education and tranining on competency bases.

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀፅ 12(1)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**
ይህ አዋጅ "የድሬዳዋ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 19/2004 ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "አስተዳደር" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፣
2. "ካቢኔ" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ነው፣
3. "ኤጀንሲ"ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ፣የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ነው፡፡
4. "ተቋም" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በደረጃ 1፣ በደረጃ 2፣ በደረጃ 3 እና ሌሎች ገበያ ተኮር የሆኑ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ሕጋዊ ተቋም ነው፡፡
5. "ኮሌጅ" ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
   ሀ. በደረጃ 1
   ለ. በደረጃ 2
   ሐ. በደረጃ 3
   መ. በደረጃ 4
   ሠ. በደረጃ 5 እና ሌሎች የገበያ ፍላጎት መሠረት ያደረጉ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ሕጋዊ የትምህርትና የሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው፣
   ረ. "ደረጃ1፣2፣3፣4፣5" ማለት አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ውስጥ የተገለፁት የሥልጠና ደረጃዎች ናቸው፡፡

Now, THERFORE, in according with article 12/1/A of the Dire Dawa administration charter proclamation No416/2004, the Dire DAwa Administration council has promulgated this proclamation.

**PART –ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**
This proclamation may be cited as ''A proclamation to establish the technical and vocational education and training Agency of the Dire Dawa administration proclamation No 19 /2011''

2. **Definition**
In this proclamation, unless the context requires otherwise:-

**1.** ''Administration'' means the Dire Dawa Administration,

**2.** ''Cabinet'' means the cabinet of the Dire Dawa Administration,

**3.** ''Agency'' means the technical and vocational Education and Training Agency that is established as per this proclamation,

**4.** ''Institution'' means Governmental and non Governmental legal entity that provides Techinical and vocational Education Training at level 1, level 2, level 3, and other market oriented short term traninings,

**5.** ''College'' means any legal Government non Governmental college that provides Technical and vocational Education Training:-

- **a.** At level 1
- **b.** At level 2
- **c.** At level 3
- **d.** At level 4
- **e.** At level 5

and other market oriented short term trainings.

**f.** ''level 1,2,3,4,5'' means training levels that are indicated at the National Technical and Vocational Education Training competency framework.

6. "ካውንስል"ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 መሠረት የተቋቋመ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል ነው፡፡
7. "ቦርድ" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ነው፡፡

## 3.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ እና/ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ህጋዊ ተቋማት በተቋቋሙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች፣ በሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከላት እና በሌሎች የሥልጠና ማዕከላት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኤጀንሲው መቋቋም፣ አላማ፣ስልጣንና ተግባር

### 4. የኤጀንሲው መቋቋም

1. "የድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ከዚህ በኃላ "ኤጀንሲ" ተብሎ የሚጠራ የራሱ የህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለአስተዳደሩ ከንቲባ ይሆናል፡፡

### 5. የኤጀንሲው አደረጃጀት፣

1. በአስተዳደሩ ከንቲባ የሚሾም ዋና ስራ አስኪያጅ እና
2. አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡ ዝርዝር አደረጃጀቱ በድሬዳዋ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ተጠንቶ በአስተዳደሩ ካቢኔ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡

### 6. ዓላማ

ኤጀንሲው የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የአስተዳደሩን ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ እድገት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎች በአግባቡ ተደራጅተውና ጥራታቸው ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲካሄዱ ማድረግ፣

6. ''Council'' means the technical and vocational education Training council that is established under article 9 of this proclamation,
7. ''Board'' means the executive board of the technical and vocational education training of the Dire Dawa administration.

3. **SCOPE**

This proclamation shall be applicable on technical and vocational and education training institutions and colleges of the administration and /or on non Governmental legal entities, on Center of competencies and other training Centers.

## PART TWO

## Establishment of the Agency, Objective, Power and Responsibility

### 4 Establishment of the agency

1. The Dire Dawa Administration Technical and Vocational Education Training (here after referred to as ''Agency'' is here by established by this proclamation as Government institution of the administration having its own legal personality.
2. The Agency Shall be accountable to the Mayor of the administration.

### 5. Organizational Structure of the Agency

1. The Agency shall have a manager which will be appointed by the Mayor.
2. The Agency shall have necessary working sections and staff. The detail organizational structure shall be determined by the civil service Bureau of the Dire Dawa Administration.

### 6. Objective

The Agency Shall have the following objectives

1. Organize properly the Technical and Vocational Education and Trainings that enable to implement

the socio-economic development of the Administration and implement this by keeping their quality in a sustainable manner.

2. የአስተዳደሩ ህዝብ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ስልጠና ማግኘታቸውን፣ የሚሰጡትም ስልጠናዎች የሀገሪቱንና የአስተዳደሩን የልማት ዕቅድና የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን መከታተል፣
3. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምርምርና ሥልጠና የሚያጎለብት አስተዳደር አቀፍ አቅም መገንባት፣
4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

## 7. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂና መርሃ-ግብር በአስተ ዳደር ደረጃ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ወቅታዊ እቅዶችን እንደዚሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን የሚያጎለብቱ ፕሮጀክ ቶችን ያዘጋጃል፣ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የሙያ ደረጃዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
3. በሚወጣው በአገር አቀፍ መመሪያ መሠረት የመካከለኛ ደረጃ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች በአስተዳደሩ ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣
4. በኤጀንሲው የሚዘጋጁ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚዘጋጁ ሥርዓተ ስልጠና በአስተዳደሩ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ሀ. መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ወይም አጫጭር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን በሚመለከት ሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

2. It shall supervise that the people of the administration has obtained training fairly, and hence these trainings should be based on the development plan of the country and the administration as well as on the need of the trained man power.
3. Build capacity at the administration level to enhance research and training at the sector of technical and vocational education training.
4. Make Technical and Vocational Education Training institutions transfer of technology and innovative centers.

## 7. Power and Function of the Agency

The agency shall have the following power and function.

1. Based on the National Technical and Vocational Education Training strategy and program shall prepare periodic plans that enables to implement at the administration level as well as projects that enable to strengthen the technical and vocational education training, and implement the same when approved,
2. Ensure the implementation of the technical and vocational education training competency standards which are enacted at National level,
3. Verify the establishment of middle level technical and vocational education training programs in the administration based on the directive that will be enacted at National level,
4. Implement training programs of technical and vocational education training which is prepared by the agency in the administration,

a. Prepare, implement and supervise curriculum in relation to regular and irregular or short term technical and vocational education trainings,

ለ. በአስተዳደሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት እና ኮሌጆች በገበያ የሥልጠና ፍላጎት መሠረት አዳዲስ የሥልጠና መስኮችለመክፈት ሲፈልጉ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

5. የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲመሩባቸው የወጡ ወይም የሚወጡ መመሪያዎች በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙና በሚቋቋሙ የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠ ራል፣

6. የማሠልጠኛ ተቋማትን እውቅና አሰጣጥ በሚመለከት የሚወጡ አገር አቀፍና የአስተዳደሩ መመሪያዎችን በአስተዳደሩ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፣

7. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን ጥራት እና ብቃት ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

8. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማዕከላት እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

9. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥን በሚመለከት አገር አቀፍ መመሪያን በአስተዳደሩ ውስጥ በሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

10. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከማምረቻና ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ከእንዱስትሪው ጋር ተቀናጅተው የትብብር ስልጠና በተገቢው መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣ያስተባብራል፣

11. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከአስተዳደሩ የልማት ዕቅድና የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መልኩ መካሄዳቸውን ይከታተላል፣

b. Issue a license to technical vocational education trainings colleges which are found in the administration to open new training programs, based in market training needs.

5. Monitor the implementation of directives enacted or which will be enacted to direct training institutions which are found and to be established in the administration,

6. Implement directives enacted by the administration or at National level in relation to accreditation of training institutions in the administration.

7. Follow and control the quality and the capacity of the technical and vocational education trainings which are conducted in the administration.

8. Provide appropriate cooperation with concerned stakeholders to make technical and vocational education training institution center of innovation and transfer of technology.

9. Based on the National directive pertaining to the issuance of evidence for the accomplishment of the technical and vocational, education and training, it shall insure its implementation in technical vocational trainings which are conducted in the administration,

10. Provide necessary support and cooperation for the proper implementation of internship and integrate Technical and Vocational Education Training with production and service provider’s institution and with industries.

11. Follow the technical and vocational and education programs which are conducted in the administration

are consistent with the development plan and need of man power of the administration.

12. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ከአስተዳደሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ የሚያስችሉ የሥራ ገበያ ፍላጎትና ሌሎችንም ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል፣ የጥናትናምርምር ውጤቶች ቤተመረጃ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ክፍት ያደርጋል፣

13. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታ ማነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የድህረ ስልጠና ክትትል ያደርጋል፣የድህረሥልጠናጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

14. በአስተዳደሩ ውስጥ በሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣በዚህ ረገድ የሚቀየሱ አገርአቀፍ አቅጣጫዎች በአስተዳደሩ ውስጥ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣

15. በአስተዳደሩ ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለሚሰጡ ተቋማትና ኮሌጆች የደረጃ ብቃት ማረጋገጫና የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በሚወጣው ደንብ መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑትንና የሥልጠና ጥራት ላይ ችግር ያለባቸውን ኮሌጆች እና ተቋማት የዕውቅና ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

16. የአስተዳደሩን የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ፣ እንዲሁም ቦርዶች በአስተዳደሩ ኮሌጆችና በተቋማት ደረጃ በህግ መሠረት መቋቋማቸውን ይከታተላል ፣አደረጃጀትንና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከተው ያቀርባል ፣የሥልጠና አካሄዳቸ ውንም ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

12. Conduct, cause to conduct and introduce study and researches on market oriented jobs and others that can solve problems in order to make technical and vocational education training programs consistent with the socio economic and need of man power of the administration. It shall organize information Center based on the result of study and the research, make it open for beneficiaries.

13. Follow post training and conduct a survey after training in order to Insure the impact of the technical and vocational education training programs which are conducted in the administration,

14. Facilitate conditions to provide special attention to disabled and women in the technical and Vocational education training programs which are conducted in the administration. Insure the implementation of National directions enacted in this relation in the administration,

15. Issue level of competency and accreditation license for institutions and colleges that provide technical and vocational education training based on the regulation which will be enacted shall cancel the accreditation license of those who are below the standard and institutions having a problem in the quality of the training,

16. Manage, coordinate Government technical and vocational training colleges of the administration and follow the legal establishment of boards in colleges and institutions in the administration. Follow and supervise their training procedures, study their organizational structure and their administration and submit to concerned organ for improvement.

17. በአስተዳደሩ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እና ተቋማት ዲኖችንና ምክትል ዲኖችን የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድና ብቃትን በመገምገም የየኮሌጁ ቦርድ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ለአስተዳደሩ ከንቲባ አቅርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል፡፡ በሥራ አፈፃፀም ብቃት ማነስ፣ወይም በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ዲኑን ወይም ምክትል ዲኖቹን ከኃላፊነት ማሰናበት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ከሥራ አግዶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለአስተዳደሩ ከንቲባ ከአስተያየት ጋር ያስተላልፋል፣

18. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የምርት ማዕከላትን በማቋ ቋምና የገቢ ማዳበሪያ ሥርዓት በመዘርጋት የውስጥ ገቢያቸውን የሚያዳብሩባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣

19. የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በሙያቸው ተደራጅተው ወደ ሥራ በሚገቡበት ጊዜ ያላቸውን የሙያ ክፍተት በመለየት ከሚመለ ከታቸው ጋር በመቀናጀት በየደረጃው ሙያዊ እገዛ እንዲደረግላቸው አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ያደርጋል፣ እገዛ መደረጉን ይከታ ተላል፣

20. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ያስተባብራል፣

21. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የለውጥ ሥራዎች ላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚሰለጥኑ ባለሙያዎች የጨበጡትን ዕውቀት ለሚመለከታቸውፈፃሚ ባለድርሻዎች ማስተላለፋቸውን ይከታተላል፣

22. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ የግል ባለሀብቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ መንግ ሥታዊ ከሆኑና ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት ይዘረጋል፣ ያበረታታል፣ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

23. በአስተዳደሩ ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ስርጭት የተመጣጠነ መሆኑን ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ተጨማሪ ተቋማት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

17. Cause to appoint Deans and Deputy Deans of the Technical and Vocational Education Training colleges of the administration, by evaluating their academics backgrounds, work experience and competency, upon comments given by the board of the colleges and submit to the Mayor for appointment. If it becomes necessary to terminate the Dean or the Deputy Deans from their responsibility based on lack of competency or lack of professional ethics, the Agency Shall suspend them by submitting his comment to the Mayor in relation to the decisions.

18. Facilitate to enhance internal revenue of Technical and vocational concerned bodies to bridge the gaps of Technical and Vocational Education Training institutions and colleges

19. Follow and provide necessary working cooperation and create network with Concerned bodies to bridge the gaps of technical and Vocational graduates when they organize themselves to enter in to jobs.

20. Prepare and coordinate a plate form in collaboration with concerned bodies to sensitize the community on Technical and Vocational Education Training.

21.Follow the dissemination of knowledge obtained by expertise in domestic and abroad on Technical and Vocational Education Training to the concerned implementing stake holders,

22. Facilitate conditions to private investors who are found in the administration to participate in the technical and vocational and education sector. It shall create strong relationship, encourage and provide comprehensive support to Governmental and Non Governmental Technical and Vocational Education Training institutions and colleges,

23. Follow the evenly distribution of the technical and vocational education training institutions and colleges of the administration in consultation with concerned bodies, it shall facilitate a condition for the establishment of additional institutions,

24. በአስተዳደሩ ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች እንዲሁም ከሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የልምድ

ልውውጥ ያደርጋል፣የጋራ ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይፈራረማል፣

25. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆችና ተቋማት ከተለያዩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር እና የኩባንያ ውስጥ ሥልጠና እንዲፈራረሙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ይከታተላል፣

26. ከትምህርት ስርአቱ ጋር የተጣጣመ አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ከአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣

27. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለሀገር አቀፍ ደረጃዎች ፣መመሪያዎች፣ እስትራቴጂዎችና መርሃግብሮች የተቀናጀ አፈጻጸም የአስተዳደሩን ድርሻ በሚመለከት ከአገር አቀፉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ጋር እንደየአግባቡ ተቀናጅቶ ይሰራል፣

28. የካውንስሉ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል፣

29. የሥራ ዕቅዱንና በጀቱን ያዘጋጃል፣በሥራ አስፈፃሚው ቦርድ ሲጸድቁም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ወቅታዊ የተግባርና የበጀት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ለአስተዳደሩ ከንቲባ ያቀርባል፣

30. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ የሆነ ምርትና አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የእንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ያስተገብራል፣

31. የተፈቀደለትን በጀት ያስተዳድራል፣ውል ይዋዋላል፣መክሰስ መከሰስ ይችላል።

32. ዓላማውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

24. Conduct experience sharing by creating relations with technical and vocational education training institutions and colleges which are found in the administration and with similar institutions that are found in domestic and abroad,

25. Provide necessary support and follow up to technical and vocational education training colleges and institutions to create cooperation and company training with different Governmental and Non Governmental organization..

26. It shall work together with the education Bureau of the administration for the consistent implementation of the education system,

27. It shall work together as may be necessary with the national technical and vocational Education training agency for the integrated implementation of national standards, directives, strategies and programs of the technical and vocational education training sector,

28. It shall serve as secretariat of the council,

29. Prepare its plan and budget, cause to implement when endorsed by the executive board, submit its physical and financial periodic reports to the Mayor of the administration,

30. It Shall cause to implement the industry extension service by creating integration with concerned bodies in order to enable Micro and Small Enterprises to provide competitive product and services in the market,

31. It Shall administered its allotted budget, can make a contract and can sue and be sued,

32. Implement other activities to implement its Objectice

## 8. የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣
2. ኤጀንሲውንበበላይነትይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
3. የኤጀንሲውንስትራቴጂክየፖሊሲሀሳቦችንቀርጻል፣ያዘጋጃል፣እን ዲፀድቅ ለአስተዳደሩ ከንቲባ ያቀርባል፣
4. በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኖች አስተዳደር ህግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
5. የኤጀንሲውን የሥራ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በጊዜው ያቀርባል፣
6. የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
7. . ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍናና በተፈለገው መጠን የሥራ ፍጥነትን ለመጨመር ከተግባሩ በከፊል ለበታቹ ላሉ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፣
8. በአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ለኤጀንሲው በተፈቀደ በጀትና ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
9. ከሦስተኛወገንጋርበሚደረግ ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፣
10. ከአስተዳደሩ ከንቲባ የሚሰጡት ተጨማሪና ተዛማጅ ሥራዎችን ይፈፅማል፣

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>የካውንስሉ መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር</u>**

## 9. <u>የካውንስሉ መቋቋም</u>

የአስተዳደሩ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ካውንስል ከዚህ በኂላ ‹‹ካውንስል›› ተብሎ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቋሚል፡፡

## 10. <u>የካውንስሉ አደረጃጀት</u>

ካውንስሉ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡

1. በአስተዳደሩ ከንቲባ የሚሰየሙ የተለያዩ አካላት ተወካዮች በአባልነት የሚገኙበት የካውንስሉ ጉባኤ፣እና

## <u>8. Power and Function of the Manager</u>

The Manager of the Agency shall have the following power and functions.

1. Implement the powers and functions of the agency indicated under article 7 of this proclamation,
2. Direct, coordinate and supervise the agency,
3. Design, prepare strategic policy ideas of the agency and submit it to the Mayor of the administration for approval,
4. Recruit, administer and terminate employees as per the law of the civil service of the administration,
5. Submit timely its report to the concerned body,
6. Prepare annual work plan and budget, shall cause to implement when approved
7. Delegate part of his duties to lower heads and other workers to the extent of necessary to enhance the efficiency of the agency,
8. Utilize the finance as per the allotted budget and plan of the agency complied with the finance administration law of the administration,
9. Represent the agency in its all dealing with third parties,
10. Carryout other additional related tasks assigned to him by the Mayor of the administration,

**<u>PART THREE</u>**

**<u>ESTABLISHMENT OF THE COUNCIL, STRUCTURE, OBJECTIVE, POWER AND FUNCTION</u>**

**9. <u>ESTABLISHMENT OF THE COUNCIL</u>**

The technical and vocational education training council of the administration (here in after referred to as the ‘’ Council’’ is here by established by this proclamation.

**10.<u>Structure of the council</u>**

The Council shall have the following structure

1 ongress of the council consisting of different representative bodies nominated by the Mayor of the administration and,

2. የካውንስሉ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ይኖሩታል፡

## 11. <u>ዓላማ</u>

ካውንስሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በአስተዳደሩ ያለውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ፣የሥልጠና ዓይነቶች፣ ደረጃዎች፣ አመራርና አደረጃጀት ከማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አኳያ መጣጣሙን በመገምገም አስፈላጊ ማሻሻያዎች ማድረግ እና ሌሎች ተጨማሪ የሥልጠና ተቋማት እንዲቋቋሙ አቅጣጫ ማስቀመጥና ማመቻቸት፣
2. የሥልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታማና የተሳካ እንዲሆኑ ሁሉም የባለድርሻ አካላት በፖሊሲና ዕቅድ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የሚሳተፉበት የምክክር መድረክ እንዲኖር በማድረግ በቅንጅትና በመደ ጋገፍ የሚሠሩበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 12. የካውንስሉ ሥልጣንና ተግባር

1. ኤጀንሲው በዓላማው መሠረት ለሚያደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ምክር ድጋፍና አመራር ይሰጣል፣
2. ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚወጡትን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በድሬዳዋ አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት ለማፋጠን የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም ስልቶች ላይ ለኤጀንሲው ምክር ይሰጣል፣ሲወሰንም ለአፈፃፀማቸው ድጋፍ ይሰጣል፣
3. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ዕቅድና ሪፖርት በመመርመር ምክር ይሰጣል፣
4. የሥልጠና መስኮች በሀገር አቀፍ የልማት ዕቅድ በአጠቃላይ እና በአስተዳደሩ የሰው ኃይል ሥልጠና ፍላጎት ወይም ገበያ ፍላጎት መሠረት በማድረግ እንዲካሄድ ስልት ይቀይሳል፣ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣

2. Executive board of the council

## 11. Objective

The council shall have the following objectives.

1. Evaluate and make necessary improvements on the technical and vocational education and training programs, standards, management and organizational structure of the administration consistent with the socio economic development, design and facilitate a direction for the establishment of other additional training institutions,
2. Create a consultative platform for stake holders to participate in policy and plan related issues to make the training programs effective and successful.

## 12. Power and Function of the Council

1. Provide advice, assistance and direction for practical activity carried out based on its objective by the agency,
2. Provided advice to the agency on policies, strategies, proclamations, regulations and directives of technical and vocational education and training sector enacted at Federal level, provide support for its implementation, design implementation strategy to promote the progress of Technical and Vocational Education Training based on the context of the Dire Dawa administration
3. Review and provide advice on the plan and report of the technical and vocational education training sector,
4. Desing a strategy, provide advice and support as to the types of training to be complied with the National plan in general, and the human resource need of the administration or market oriented,

5. በመደበኛም ሆነ መበኛ ባልሆነ፣ በየደረጃው ያሉ ሥልጠናዎችን በማጠናቀቅ የሚወጡትን ሠልጣኞች ከሥራ ሥምሪት አኳያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት የማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ፣ የድሬ ብድርና

ቁጠባ ተቋም፣የቤቶች ልማት ፕሮጀክት እና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ለሚያከናውኑት ተግባር እገዛ ይሰጣል፣

6. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመምከር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣
7. የኤጀንሲው ዓላማን ስኬት የሚያጎለብቱ ምክርና ድጋፎችን ይሰጣል።
8. ዓላማውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 13. የካውንስሉ አባላት

የካውንስሉ ጉባኤ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ…………………...........ሰብሳቢ
2. የድሬዳዋአስተዳደርንግድ፣ኢንዱ፣ኢን/ቢሮኃላፊ…...ም/ሰብሳቢ
3. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ…………….............. ጸሐፊ
4. የድሬዳዋአስተዳደርሴቶች፣ወጣቶችናህፃናትቢሮኃላፊ…....አባል
5. የድሬዳዋ አስተዳደር ገ/ኢ/ል/ቢሮ ኃላፊ………………...አባል
6. የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ…………………....አባል
7. የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ…………………አባል
8. የድሬዳዋ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ……………....አባል
9. የድሬዳዋአስተዳደርፍትህፀጥታናሕግጉዳዮችቢሮኃላፊ...….አባል
10. የድሬዳዋ አስተዳደር ግብ/ውሃ ማዕ/ኢ/ቢ/ኃላፊ…........…አባል
11. የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ኃላፊ…………....አባል
12. የድሬዳዋ አስተዳደር የመን/ኮሙ/ጉ/ቢሮ ኃላፊ………….አባል
13. የድሬዳዋ ከተማ ሥራአስኪያጅ ጽ/ቤት………………....አባል

5. Provide assistance to coordinated effort of technical and vocational education and training sector, Micro and small scale enterprises, cooperative societies promotion and development, Dire Micro Finance Institutions and Housing Development project and other concerned bodies connection with employment opportunity for trainees that accomplish their training in formal and non formal programs of trainings At different stages.
6. Facilitate favorable conditions by consulting on technical and vocational education training related issues and follow their implementation.
7. Provide advice and support to strengthen the achievement of the agency's objective
8. Implement other activities necessary to perform its objective.

## 13. Members of the Council

The Assembly of the council shall have the following members.

1. Mayor of the Dire Dawa Administration ….. Chairperson
2. Head of the Trade, Industry and Investment Bureau of the Dire Dawa administration ……….….Deputy chairperson
3. Manager of the Agency …..…….. ………… secretary
4. Head of women, youth and children Bureau of the Dire Dawa administration ………………………… Member
5. Head of Finance and Economic Development Bureau of the Dire Dawa administration ……….……… Member
6. Head of Education Bureau of the Dire Dawa administration ………….…………………… Member
7. Head of Health Bureau of the Dire Dawa administration ………………………………………...… Member
8. Head of Civil Service Bureau of the Dire Dawa administration…………………………………Member
9. Head of Justice, Security and legal Affairs Bureau of the Dire Dawa Administration ………..….…. Member
10. Head of Agriculture, water, mining and Energy Bureau of the Dire Dawa administration ……….,……Member
11. Head of the Sport Commission of the Dire Dawa administration ……………………………… Memeber
12. Head of Government communication affairs Bureau of the Dire Dawa administration ……………..… Member
13. Manager of ther Dire Dawa City….……….... Member

14. የድሬዳዋ አስተዳደር ጥቃ/አነ/ን/ሥራ/ኤ/ኃላፊ……...አባል
15. የድሬዳዋ ወጣቶች ፌዴሬሽን ፕረዝዳንት…….........አባል
16. ምሥራቅ አፍሪካ ቦትሊንግ ካምፓኒ ድ/ዳ/ቅ……….አባል
17. የድሬዳዋ ኢንዱስትሪዎች ማህበር………….……..አባል
18. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድ/ዳ/ቅርንጫፍ……….......አባል

19. የድሬ/አስ/ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት……....አባል
20. መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን የምሥ/ቅርንጫፍ……..አባል
21. የድሬዳዋ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ኃላፊ…..አባል
22. የድሬዳዋ አስተዳደር ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ኃ/….አባል
23. የግል ኮሌጆች ተወካይ…………………………..….አባል
24. የድሬዳዋ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ዲን…….………..አባል
25. የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት……………………አባል
26. ትዮ-ጣሊያን ትብብር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ………..አባል
27. ኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት…………….…አባል
28. መደበኛ ያልሆነ የቴክ/ሙያ ተቋማት ተወካይ……..አባል
29. የድሬዳዋ ምግብ ኮፕሌክስ አክሲዮን ማህበር……..…አባል
30. ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ………………………...…አባል
31. የድሬዳዋ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን……......አባል
32. የኢትዮ ቴሌኮም ምሥራቅ ሪጅን…………………..አባል
33. ናስ ፉድስ ፋብሪካ…………………………………..አባል
34. ቸሻየር ሰርቪስ ኢትዮጵያ ድ/ዳ/ቅ/ጽ/ቤት…………...አባል
35. ድሬ ብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር……………..አባል
36. ሌሎችእንደአስፈላጊነቱ በካቢኔው የሚሰየሙ…..አባልሎች

## 14. የካውንስሉ፣ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

1.ካውንስሉን በሰብሳቢነት ይመራል፣

2.የካውንስሉን ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

3.የአስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሚመለከት በማናቸውም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ላይ አስተዳደሩን ይወክላል፡፡

14. Head of the Micro Small and Enterprise agency of the Dire Dawa administration. ……………..……. Member
15. President of the youth Federation of Dire Dawa ……………………………..……………… Member
16. East Africa Bottling Company of the Dire Dawa Branch ……………………………………………….. Member
17. Association of industries of the Dire Dawa administration …..…………………………... Member
18. Ethiopian Commercial .Bank of Dire Dawa Branch.............................................................. Member
19. HIV AIDS protection and Control office of the Dire Dawa administration …………….. Member
20. Ethiopian Electric Power Corporation Eastern Branch ……………………………….... Member
21. Head of Water and sewerage Authority of the Dire Dawa City ……………………..…. Member
22. Head of the Housing Development project of the Dire Dawa Administration … ……....… Member
23. Representative of Private Colleges …... ...Member
24. Dean of the Dire Dawa Technical and Vocational College …………………………….. ..Member
25. President of the Dire Dawa University……... ………………………………………..Member
26. College of the Ethio- Italy Technical and Vocational Cooperation ………………………………..… Member
27. Cooperation of the Ethio Djibouti Rail Way ……..…Member
28. Representative of informal training of Technical and VocationalInstitutions………………….……... Member
29. Dire Dawa Food Complex Share Company …….. …………………………………………………Member
30. National Cement Factory ………………………. Member
31. Road Authority of the Dire Dawa Administration …… …………………………………………………Member
32. Ethio Telecom Eastern Region …………………. Member
33. Factory of Nas Foods …………………….…. Member
34. Ethiopian Cheshire Service Dire Dawa Branch Office. …………………………………………………Member
35. Dire Micro Finance Share Company……………. Member
36. Others nominated by the cabinet as may be necessary... …………………………………………………Member

## 14. Power and Function of the Chairperson of the Council

1. Direct the Council as a chairperson,
2. Insure the implementation of the decision of the council,
3. Represent the administration on issues related to the Technical and Vocational and Education Training on any meeting and assembly,

## 15. የካውንስሉ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

1. የካውንስሉ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ስብሰባውን በበላይነት ይመራል፣
2. በካውንስሉ ሰብሳቢና በካውንስሉ የሚሰ ጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

## 16. የካውንስሉ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር

1. የካውንስሉን ጉባኤ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

2. የካውንስሉን የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ ሪፖርትም ያዘጋጃል፣
3. በካውንስሉ ሰብሳቢና በካውንስሉ የሚሰ ጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**17. የካውንስሉ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና የሥራ ዘመን**

1. የካውንስሉ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም በምክትል ሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል፣
2. ካውንስሉ በየሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
3. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
4. ሰብሳቢውን ጨምሮ ከካውንስሉ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣
5. ካውንስሉ ውሣኔ የሚያስተላልፈው በድምጽ ብልጫ ነው። ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የካውንስሉ ውሣኔ ይሆናል፣
6. ከዚህ በላይ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ካውንስሉ የራሱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ማውጣት ይችላል፣
7. የካውንስሉ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

**ክፍል አራት**

**የስራ አስፈፃሚው ቦርድ መቋቋም፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር**

**18. የካውንስሉ ስራ አስፈፃሚ ቦርድመቋቋም**

የካውንስሉ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ከዚህ በኋላ ‹‹የካውንስሉ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ›› ተብሎ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**15. Power and Function of the Deputy Chair person of the Council**

1. Direct the Meeting of the council in the absence of the chairperson of the Council,
2. He/she perform other tasks assigned to him/her by the chairperson.

**16. Power and Function of the Secretary.**

1. Prepare Agendas of the council's meeting,
2. Take minutes for the meeting of the council and prepare reports,
3. Perform other tasks assigned to him by the chairperson and Deputy Chairperson of the council.

**.17. Meeting Procedure and Tenure of the Council**

1. Meeting of the council may be called by the chairperson or Deputy chairperson of the council ,
2. The Council shall conduct a regular meeting once in every three months,
3. A meeting may be called at any time when ever urgent cases a rises,
4. There Shall be a quorum where more than half of the members of the council including the chairperson are present in the meeting,
5. Pass decisions by a majority vote. However, when votes are in tie, the idea supported by the chairperson shall be the decision of the council,
6. Without prejudice to the provisons set out under this article, the council may issue its own meeting procedure,
7. The tenur of the council shall be two years,

**PART FOUR**

**Establishment of the Executive Board, Objective and Power and Function**

**18. Establishment of the Executive Board,**

The executive board of the council here in after refered to '' executive board of the council'' is here by established by this proclamation.

**19. ዓላማ**

የካውንስሉ ስራ አስፈፃሚ ቦርድ ዋና አላማ የኤጀንሲውን የሥራ አፈፃፀም በየጊዜው እየገመገመ የትኩረት አቅጣጫዎችን ማመልከት ነው።

**20. የካውንስሉ ስራ አስፈፃሚ ቦርድ የሥራ ዘመን እና አባላት፡-**

1. የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ለካውንስሉ ተጠሪ ሆኖ አባላቱ ሰባት ይሆናሉ፣

2. የካውንስሉ ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ፣እና ፀሐፊ የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ሆነው በካውንስሉ ጉባኤ ያላቸው ኃላፊነት እንደቅደም ተከተላቸው ይኖራቸዋል፣
3. ሌሎች የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት በአስተዳደሩ ካቢኔ የሚወሰኑ ይሆናሉ፣
4. የስራ አስፈጻሚ ቦርድ የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

**21. <u>የካውንስሉ ስራ አስፈፃሚ ቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>**

የስራ አስፈጻሚ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. የካውንስሉን ጉባኤ የስብሰባ አጀንዳዎች አስቀድሞ በመመርመር ያጸድቃል፣
2. የካውንስሉ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
3. የካውንስሉ ፀሐፊ ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር የሚያቀርባቸውን አስቸኳይ ጉዳዮች ተመልክቶ የካውንስሉ ጉባኤ በማይሰበሰብበት ጊዜ ውሳኔ ይሰጣል፣
4. የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም የሙያ ደረጃውን ለመወሰን ምቹ ሁኔታ ዎችን ያመቻቻል፣ትምህርትና ሥልጠና ነክ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳብ ይሰጣል፣ውጤታቸውንም በመፈተሽ ተግባራዊ እንዲሆኑ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
5. በአስተዳደሩ የሚካሄደው የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሀገር አቀፍ ፕሮግራም መነሻ በማድረግ በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የተዘጋጀ የራሱ የሆነ ስትራቴጂ ኖሮት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
6. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሌሎች ባለድርሻ አካላት እና የአሰልጣኝ አካላት መደጋገፍ ምቹ ሁኔታ እንዲኖር ያደርጋል፣
7. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አኳያ የሥልጠና ዕውቅና ዕድሳት ማስፋፋትና ምትክ አሰጣጥ ተግባራትን ይመረምራል፣ኢንቨስትመንት የሚስፋፋበትን ሃሳብ ያቀርባል፣

**<u>19. Objective</u>**

The main objective of the executive board of the council is to set a direction by evaluating the performance of the agency periodically.

**20. <u>The tenur of the executive board of the council and its members</u>**

1. The executive board of the council shall have seven members which are accountable to the council.
2. The chairperson, the deputy chairperson and the secretary of the council shall be members of the executive board of the council, and shall have similar power that they have in the council respectively,
3. Other executive members of the board shall be determined by the cabinet of the administration.
4. The tenur of the executive board shall be two years.

**21. <u>POWER and Functions of the Executive Board of the</u>**

The executive board shall have the following power and Funcition

1. Approve the meeting agendas of the assembly of the council up on prior investigation.
2. Follow the implementation of the council's assembly decision.
3. Render a decision on urgent issues submitted to it by the secretary and the chairperson after consultation; follow its implementation by the agency.
4. Facilitate a condutive atmosphere to set vocational standard using different evaluation methods, and recommend a solution on study and training, put direction for its implementation by assessing their outcomes.
5. Based on the national program, it shall have a strategy of technical and vocational and education training of the administration which is prepared with the participation of stakeholders and cause its implementation.
6. Create a couducive atmosphere to have support by trainer organs and Other stakeholders on technical and vocational and education training program.
7. Investigate and accreditation, renewal, promotion and replacement on provision of activities of training on technical and vocational and education training.

8. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማጠናቀቂያ እና የሙያ ብቃት ምዘና ወይም ክህሎት ምዘና በተገቢው መንገድ መተግበሩን ክትትል ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የሥልጠና ፕሮግራሞች ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ይከታተላል፣

9. ለሥርዓተ ትምህርቱ ትግበራ መሻሻልና ለሥልጠና ጥራት መረጋገጥ የባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ድጋፍ እንዲያገኙና ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፣
10. የሥልጠናው ግብዓት ማለትም የአሠልጣኝን አቅም መገንባትን፣ የማሰልጠኛ መሣሪያዎች መሟላትን፣ በአጠቃላይ የማሰልጠኛ ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ለተግባራዊነቱም ድጋፍ ይሰጣል፣
11. ከሥልጠና ይዘት አኳያ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወሳኝ ድርሻ ያለው ኢንተርንሽፕ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው አሳታፊ በሆነ መልኩ ደንብ እንዲወጣለት አሰሪዎችን እና በአጠቃላይ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ጥረት ያደርጋል፣
12. የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት በተለይ የመንግሥት የሆኑት ገቢያቸውን እንዲያዳብሩ ወጪ ቆጣቢ ስልት እንዲከተሉ የወጪ መጋራት አሰራርን በፌዴራል መንግሥት ከተዘጋጀው ስትራ ቴጂ በመነሳት ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ እንዲሆን ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣የአፈፃፀም አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
13. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናት የሚዘጋጁ ፕሮጀክቶችን በመመርመር አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣል፣
14. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በድህረ ሥልጠና የሥልጠና መስኮች በሥርዓተ ትምህርት ይዘትና ትግበራ እና በሥራ ገበያ ሁኔታ የታለመላቸውን ግብ መምታታቸውን ለማረጋገጥ ተግባራዊ መሆ ናቸውን ይከታተላል፣በሚገኘውም የግምገማ ውጤት መሠረት ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀ ምጣል፣

8. Follow the proper implementation for the accomplishment of the Technical, Vocational, Education and Training and the evaluation of professional competency or skill appraisal, generally follow the implementation of the training programs are complied with their standards.

9. In order to insure the quality of training and to improve the implementation of the curriculum, coordinate stakeholders, provide a support and create conductive atmosphere to them
10. Set a direction that the training inputs meaning building the capacity of the trainers, the fulfillement of the training material, in general that the training institution shall be complied with the standards and provide a support for its implementation.
11. It shall exert an effort and provide a support and for its complete implementation with participation and in collaboration with employers and stakeholders in general that intermship to have a legal framework and enact a regulation on it which has a key role on technical and vocational education training.
12. Adopt the strategy prepared by the Federal Government in the context of the administration to enhance their income, to be cost effective and to develop cost sharing by those Governmental institutions of the technical and vocational and education training and hence provide a support, advice and set a direction for its implementation.
13. Set a direction by evaluating project studies prepared by technical vocational and education training, and provide a support for its implementation when approved.
14. Follow the implementation and achievement of goals on Technical and Vocational and Educational Training post (after) training on the fields of the training, on the content of the Curriculum and its implementation, based on this evaluation result, set a future direction.

15. የካውንስሉን የሥራ እንቅስቃሀ በተመለከተ በየሩብ ዓመቱ በሰብሳቢው አማካይነት ለአስተዳደሩ ካቢኔ ሪፖርት ያቀርባል፣
16. ዓላማውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

22. የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሀፊ ስልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ የተደነገገውየካውንስሉ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሀፊ ስልጣንና ተግባር ለካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሀፊ ተፈ ሚነት ይኖረዋል ፣

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23. የበጀት ምንጭ

የኤጀንሲው በጀት ከሚከተሉት ሊገኝ ይችላል፡-

1. ከድሬዳዋ አስተዳደር የሚመደብ በጀት፣
2. ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ እገዛ፣

### 24. የሂሣብ መዛግብት አያያዝ

1. ኤጀንሲው ትክክለኛ የሆኑና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል።

### 25. የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆችን በሚመለከት የአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ከነበረው የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፤
2. የአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ለኤጀንሲው የተላለፉትን መብትና ግዴታዎች አስመልክቶ ያሉትን መዛግብት፣ ሰነዶችና ሌሎች መረጃዎች ለኤጀንሲው ያስረክባል።

15. Submit the performance report of the council quarterly to the cabinet of the administration by the chairperson.b
16. Implement other necessary activities to achieve its objective.

**22. power & function of the Executive board of the cuncile chair personDeputynchairperson secretary.**

The power & function of the chair person Deputy chair person and Decretary of the council provided her in shall be applicable on the Exective board of chair person Deputy chair person and secretary

## PART FIVE

## MISCELANEOUS –PROVISIONS,

### 23 . Source of Budget

he budget of the agency shall be the following,

1. Budget that is allotted by the Dire Dawa administration,
2. Supports obtained from Governmental and Non Governmental organizations.

### 24. Handling of Financial Records

1. The agency shall handle accurate and complete financial accounts,
2. Books of account of the agency shall be audited by the chief auditor of the administration

### 25. Transfer of Rights and Obligations,

1. The Rights and obligations that had acquired by the Education Bureau of the administration in relation to coordinate and Direct the technical and Vocational Education Training Institutions and colleges are here by transferred to the Agency
2. Based on the Rights and Obligations transferred to the agency as per sub article 1of this article, the Education Bureau of the Administration shall handover documents, records and other evidences to the Agency.

### 26. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ካቢኔው ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

### 27. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

1. የድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 2/2001 እና የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን

የወጣው አዋጅ ቁጥር 16/2003 አንቀፅ 14 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**28. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ትሬ□□ ጥቅምት 30 ቀን 2□□4 □ም**

**አሰድ ዚያድ**

**የድሬደዋ አስተዳደር ከንቲባ**

## 26. Power to Issue Regulation.

The cabinet may issue regulations to implement this proclamation.

**27 Repealed and Inapplicable Laws**

**1.** The Dire Dawa administration Technical and Vocational Education and Training council establishment Regulation No 2/2009 and proclamation to re-establish the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration proclamation No 16/2010 Article 14 are here by repealed.

**2.** Any Proclamation, Regulation, Directive or Customery practice which are inconsistent with this proclamation shall have no effect on matters covered under this proclamation

## 28. Effective Date

this proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dire Dawa this 10th day of october, 2011**

**Assed Ziyad**

**Mayor Of the Dire Dawa Administration**